# ዳግም የ "ራዕይ" እጦቱ ደዌ እንዳይጠናወተን !።

## ይድረስ ለ-ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መሪዎች!! ባላችሁበት፤

*ሸዋንዳኝ መላኩ (ካፒቴን)*
*(Johannesburg, RSA)*

ውድ የቅንጅቱ አመራሮች ! በቅድሚያ ሕዝብ የጣለባችሁን አደራ ላለማስነካት በጽናት ቆማችሁ በመታገላችሁና በሳቢያውም ለከፈላችሁት መስዋዕትነት ያለኝን አድናቆትና ክብር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ .....!!!

እኔ የዚህች መልዕክት አቅራቢ ! በውጭው አለም አንዱ ጥግ ላይ ደኩኜ አብዛኛውን ጊዜዬን የእለት ጉርስ፤ የአመት ልብስ፤ ፍለጋ በሚደረግ ቀና ደፋ የማጠፋ፤ ኢትዮጵያዊ ወንድማችሁ ነኝ። በውጭው አለም እንደሚገኘው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ እኔም የሃገሬን ሕዝብ ችግርና ብሶት ፤ መከራና ስቃይ ፤ በሰማሁ ቁጥር በቁጭት እብሰለሰላለሁ። አዝናለሁ!! በግል ሕይወቴ ዛቢያ ላይ ስሽከረከር የወገኔን ችግር ለመጋራት ያለመቻሌ ደግሞ የጥፋተኝነት ስሜት(Guilt) ሲፈጥርብኝ ኖሯል።ይህን ስሜቴን አብዛኛው የዲያስፖራው ወገኔ እንደሚጋራኝ እገምታለሁ።

ይህ ለዘመናት በሕሊናዬ መሽጎ የቆየው የጥፋተኝነት ስሜት ከቅርብ አመታት ወዲህ በመጠኑም እየቀለለኝ የመጣ ይመስለኛል። ምክንያት፦ ለቅንጅት ድጋፍ በመስጠት ወገኔ ከሚገኝበት ችግርና መከራ ለመታደግ በሚደረግ ትግል ውስጥ ኢምንትም ብትሆን እገዛ ያደረኩ ስለሚመስለኝ ነው።"ቅንጅት መንፈስ ነው" የተባለለትም ለዚሁ፡ይመስለኛል።የህሊና ወቀሳን መፈወሻ መንፈስ.....

ቅንጅት፦ ለዘመናት በግል ሕይወቱ ውስጥ ራሱን ቀብሮ የኖረውን እኔን መሰል ዜጋ ሁሉ ከግለኝነት አዚም አላቆ ስለወገኑ እንዲያስብ አነሳስቷል። ቅንጅትን መንፈስ ያሰኘውም ይህን የተነሳሽነት ስሜት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ህሊና ለማስረጽ የመቻሉ ትንግርት ነው ። ከህሊና አስገዳጅነት የመነጨ መነሳሳት.....!

በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም ለሃገሩና ለወገኑ የመቆርቆር ስሜት የሌለው "ጨለምተኛ" ወገን ሲሉ ስያሜ የሰጡት (አብዛኛው ወጣቱ ክፍል) ከጨለምተኝነት ስሜት በአስገራሚ ፍጥነት የተላቀቀው በቅንጅት መንፈስ ነው። በሕዝብ መልካም ፈቃድ (Goodwill) ብቻ የተከወነ፦ የራዕይ ማጣትን ደዌ የፈወሰ ፈጣንና ሥር-ነቀል የተነሳሽነት መንፈስ.......!

በሕዝብ መልካም ፈቃድ የተከወነ፡ የተገነባ(የቆመ) ስንል የሕዝብ ልጆች ህይወታቸውን መስዋዕት ለማድረግ የፈቀዱለት ፤ የሞቱለት፤ የደሙለት፤ የቆሰሉለት፤ ባጠቃላይ ግፍና ስቃይ የተቀበሉለት ማለታችን ነው። በሕዝብ ልጆች ደም የተገኘ ውጤት ባለቤት ደግሞ ሕዝብ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም ።

<u>ውድ የቅንጅት መሪዎች ሆይ!</u> ወደ ዋናው ነጥብ ስንገባ፦ ዛሬ በእናንተ በቅንጅት አመራሮች መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት ይብዛም ይነስም በቅንጅት መንፈስ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳረፉ አልቀረም። የቅንጅት መንፈስ ስንል አሁንም ለሕዝብ መብት ለመታገል የመነሳሳት መንፈስ ማለታችን ነውና፦ እንዳናጣው የምንሰጋውም ይህንኑ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የተቀጣጠለውን ለሕዝብ መብት መከበር የመታገልን ቁርጠኛ ስሜት ነው፡፡ አስፈሪ ብቻም ሳይሆን አሳፋሪ የሚሆነውም ይህ የትግል ስሜት በእናንተ በመሪዎቻችን አለመግባባት ከተዳፈነ ነው።

ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት የሚሆነውም ይህ በሃገር ውስጥ ዘርና ክልል ሳይገድበው፡- በውጭው አለምም የቦታ ርቀት ሳይወስነው፡- ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሰፈረበት ሁሉ፡- ዘልቆ የተቀጣጠለው የትግል ስሜት ደብዝዞ ዳግም ጨለምተኝነቱ ከነገሰበን ነው። ጩህታችንም ለዚሁ ነው።! ዳግም የራዕይ እጦቱ ደዌ እንዳይጠናወተን !።

<u>ውድ የቅንጅት መሪዎች ሆይ!</u> የእሥርና የእንግልት መስዋዕትነት ከፍላችሁ ያሰከበራችሁትን የሕዝብ መብትና ፍላጎት ከማንም በፊት እራሳችሁ ማክበር ይገባችኋል። የሕዝብ ፍላጎት ደግሞ ልዩነታችሁን አቻችላችሁ እንደትሰሩ በመሆኑ ይህንኑ የሕዝብ ፍላጎት ተግባራዊ በማድረግ ዳግም የአላማ ጽናታችሁን ልታሳዩን ይገባል።

በአሁኑ ወቅት፡- በሳይበር የኢትዮጵያዊያን የድምጽና የጽሁፍ ውይይት መድረኮች ላይ ትኩስ አጀንዳ ሆኖ የሚንሸራሸረው ይህው በእናንተ መካከል ተከሰተ የተባለው አለመግባባት ነው። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ውይይቱ ችግሩን ወይም አለመግባባቱን ለመፍታት ምን ይደረግ? በሚለው ቁልፍ ጥያቄ ዙሪያ ያጠነጠ ጠቃሚ(Constructive) ውይይት አለመሆኑ ነው(ሁሉንም የውይይት መድረኮች ማለቴ አይደለም)። በአንዳንድ የሳይበር መድረኮች የሚደረገው ውይይት በአመዛኙ ወገንና ጎራ ለይቶ አንዱ አንዱን የመዘርጠጥ በታኝ አዝማሚያ ያለው ነው።ይህ ብቻ አይደለም አንዳንድ በጋዜጠኝነት ሙያ ውስጥ እንደሆኑ የሚገምቱ ነገርግን ሙያው የሚጠይቀው ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ብቻ ሳይሆን የሌላቸው የዜና-አውታሮችም ጭፍን በሆነ ወገናዊነት፡- ጎራ ለይተው አንዱን እየወቀሱ ሌላውን እያወደሱ አለመግባባቱ ላይ ቤንዚን ሲያርከፈክፉ ተሰተውለዋል።

በእርግጥ ልዩነቱ እንዲሰፋ የሚፈልጉ ወያኔን ጨምሮ ሌሎችም አካሎች በስውርና በረቀቀ መንገድ የሚያደርጉት ጥረት እንዳለ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ቅንጅትን እንደ ሕዝብ ወኪል የሚያየው የበርካታው ዜጋ ፍላጎት:- አለመግባባቱ በሠላም እንዲፈታ እንጂ አንዱ ጎራ አንዱን ጥሎ እንዲያልፍ የሚሻበት ምንም ምክንያት የለውም። ወገናዊነቱም ለቅንጅት እንጂ ለኢንጅነር ኃይሉ አልያም ለዶ/ር ብርሃኑ አይደለም። በመሆኑም ሚናህን ወይም ጎራህን ለይ አይነቱን በታኝ አካሄድ በተቻለን ሁሉ ልንታገለው ይገባል እላለሁ፡፡

ይህንን የጥፋት አካሄድ በአጭሩ ማረምና የተንኮለኞችን ሴራ ማክሸፍ የሚቻለው ደግሞ አለመግባባቱ ጠረጴዛ ላይ ቀርቦ በውይይት ሲበለትና መፍትሄውም ሲገኝ ነው። "People never plan to fail but fail to plan" የምትለው የእንግሊዘኛ ብሂል ጥሩ ግንዛቤ ትሰጣለች ብዬ አስባለሁ። አዎ! ውድቀትን አልሞ እቅድ የሚነድፍ የለም፤ ነገር ግን እቅድ ማውጣት ያለመቻል ወደ ውድቀት ያመራልና በስሜታዊነት ወይም በእልህ ከሚሰራ ሥራ መቆጠብ ያስፈልገናል፡፤ ዛሬ በቅንጅት አመራር ላይ የተፈጠረው አለመግባባት አፋጣኝ መፍትሄ ካልተሰጠው ሁላችንም ተሸናፊ የምንሆንበት እንጂ አንዱ አሸንፎ ሌላው ተሸንፎ የሚወጣበት የካምቦሎጆው አይነት ውጤት ሊኖር አይችልም። ከዚህ ግዙፍ እውነታ በመነሳት ውድ...... አመራሮች ሆይ፡-!ጊዜው የሚጠይቃችሁን ይህን ታሪካዊ ሃላፊነት ትወጡ ዘንድ አሁንም በድጋሚ ወገናዊ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

በመጨረሻም እንግዲህ መልዕክቴን የማጠቃልለው በኔ ግንዛቤ ወደ መፍትሄ ሊያደርሱን ይችላሉ የምላቸውን አቅጣጫዎች በመጠቋቆም ይሆናል።

1. ልዩነታችሁን ወይም አለመግባባቱን ለማስወገድ በግንባር መነጋገር ብቻ ሳይሆን ለብዙሃኑ ወገን ፍላጎት መገዛትም ግዴታችሁ በመሆኑ!! ያለማንም ጣልቃ ገብነት ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ መጥታችሁ በተለመደው የሰከነና የተጠና አካሄዳችሁ ውዝግቡን መፍታት ጊዜ ልትሰጡት የማይገባ ጉዳይ ነው፡-

2. ውይይቱም እስኪ ጀመር ድረስ አንዱ ወገን በሌላው ወገን ላይ አሉታዊ መግለጫ እየሰጠ አለመግባባቱን ወደ ማይፈታ ቅራኔ ለመለወጥ የሚሯሯጡ ተንኮለኞች በየመድረኩ የሚለኩሱትን እሳት ከማራገብ መቆጠብ ይገባዋል።

3. በውይይቱ ወቅትም አለመግባባቱ ሊፈታ የሚችል አይደለም!! የሚለው ውሳኔ እንደ መጨረሻ ውሳኔ ሊመጣ የሚችለው ወይም የሚገባው በአንድና አንድ ምክንያት ብቻ ይመስለኛል፡፡ ይህውም ከሁለቱ አንዱ ወገን ቅንጅትን ለማጥፋት ከሚንቀሳቀሱ አካሎች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት እንዳለው ሲረጋገጥ ብቻ ነው! ከዚህ መሰረታዊና የማይታረቅ ቅራኔ ውጭ በሚነሱ ጥቃቅን ልዩነቶች ምክንያት እየተመመ ያለው የትግል ባቡር መቆምም ሆነ መዘግየት አይገባውምና ቢቻል ልዩነቶቹን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ያ ካልሆነም እያንዳንዱ አመራር አባል ሃሳቡንና ፍላጎቱን ለብዙሃኑ ሃሳብና ፍላጎት ተገዥ አድርጎ ወደ መፍትሂ አቅጣጫ ለመጓዝ ፈቃዱን በማሳየት ለሕዝብ ያለውን ከበሬታና ታማኝነት በድጋሚ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል እላለሁ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የራሳቸውን ሃሳብና ፍላጎት ከብዙሃኑ ፍላጎት በማስቀደም የብዙሃኑን ሃሳብና ፍላጎት የማይቀበል(ሉ) ግለሰብም ሆነ ግለሰቦች ከታየ(ዩ) ያለምንም ማስተዛዘኛ ከሃላፊነታቸው ማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሂ ይመስለኛል።ለብዙሃን ፍላጎት የማይገዙ አምባገነኖች ናቸውና።

4. ከዚህ ውጭ በቀና ስህተትም ይሁን በባሕሪ ችግር የተፈጠሩ ጥቃቅን አለመግባባቶች ካሉም ለሕዝብ ክብር ሲባል አጥፊው ይቅርታ ጠይቆ ተበዳይም ይቅር ብሎ ተቻችሎ በመስራት ለመላው የቅንጅት ደጋፊ ኢትዮጵያዊ ወገን አርአያ መሆን ይጠበቅባችኋል እላለሁ፡፧

5. ሌላው፡- ዋና! ጉዳይ  ውይይቱ መካሄድ ያለበት በዋንኞቹ የቅንጅት አመራሮች መካከል ብቻ ይመስለኛል። ለዚህ አለመግባባት እርሾ ሆነዋል ተብለው የሚጠቀሱትን የቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራሮች በውይይቱ ማሳተፍ ችግሩንና አለመግባባቱን ከማካረረ ሌላ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። በትክክለኛውም አሰራራ ከተኬደ ቅንጅት ኢንተርናሽናል ውክልናው ለዋናው አመራር እንጂ በሕዝብ የቀጥታ ምርጫ የተቀመጠ ባለመሆኑ በዋናው አመራር ስብሰባ ተሳታፊ መሆን አይችልም።

6. በበፊቱና በአሁኑ የቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራሮች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ችግርና አለመግባባት ለዋናው የቅንጅት አመራር አለመግባባት መንስኤ ሆኖ መገኘቱ እውነት ከሆነም፡- ቅንጅት ኢንተርናሽናልን በትኖ በየክፍለ አለማቱ የተቋቋሙት የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በወኪል  የሚሳተፉበት አለም አቀፍ ስብሰባ ጠርቶ አዲስ ኢንተርናሽናል ኮሚቴ እንዲዋቀር ማድረግ ተገቢና ዲሞክራሲያዊም አሰራር ነው እላለሁ። ይህን ማደርግም በራሱ የተተበተበውን ያለመግባባት ችግርና መቆራቆስ በጣጥሶ በአዲስ መንፈስ ለመንቀሳቀስ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ።

ከዚህ በተረፈ በእናንተ አለመግባባት በግፍ የፈሰሰው የሰማዕታቱ ደም ዋጋ እንዳያጣ ታስቡ ዘንድ አደራ እያልኩ የምሰናበታችሁ ።ሰላሙንና ጤናውን አብዝቶ ይሰጣችሁም ዘንድ በመመኘት ነው። !!!

ቸሩ እግዚአብሄር ሆይ! ኢትዮጵያን አስባት!